Ethiopiawinet Radio

Ethiopiawinet.net

ግርማ ካሳ (muziky68@yahoo.com )



በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና በፕሬዝዳንት ኢሣያስ አፈወርቂ በግፍ የታሰሩ ሠላማዊ ወገኖቻችን መካከል በጥቂቱ። (ከግራ ወደ ቀኝ) ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳ፣ ፓስተር ኃይሌ ነዕዝጊ፣ ፓስተር ዶ/ር ክፍሉ ገብረመስቀል፣ ፓስተር ተስፋጽዮን ሃጎስ እና አርስቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን።

በቅርቡ የኢትዮጵያን ሪቪውዋና አዘጋጅ አቶ ኤሊያስ ክፍሌ በድረ ገጻቸው ላይ አስመራ ሆነ ውየ ተነሱትን ፎቶግራፎች ተመለከትኩ። የአስመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ የነበሩኩ ጊዜ በዚያ ያሳለፍኩትን ዓመታት ፎቶግራፎቹ አስታወሱኝ። ብዙ ጊዜ በፖስት ካርድ ላይ የምናየው፣ ዘንባባዎች በዳርና በዳር ያሉበት መንገድ የሚያልፈው፣ ፒያሳ ወይንም ኮምፖሽታቶ በሚባለው ሰፈር ነው። በዚያ መንገድ ብዙ ኬክ ቤቶችና ቡና ቤቶች ነበሩ። ትዝ ይለኛል በአምሳ ሣንቲም አንድ ኬክና ምን የመሰለ ካፑቺኖ እናዝ ነበር። በተለይም ሲመሽ ከመብራቶቿ ጋር ከተማዋ በጣም ታምራለች።

ከከተማዋ ውበት ባሻገር የማልረሳውና በውስጤየ ተተከለ አንድ ሌላ ነገር ቢኖር የህዝቡ ፈሪሃ እንግዚአብሔር እና ደግነት ነበር። እስቲ አንዳንድ ያጋጠመኝ ላጫውታችሁ። አንድ ቀን በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ወዳለው ካፍቴሪያ እራቴን ለመብላት እየሄድኩ ሳለ ጓደኞቼ አገኙኝና "አትሄድምእንዴ?" አሉኝ። "የት?" አልኳቸው። "ንግደት" አሉኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ያንን ቃል የሰማሁት። ጓደኞቼ ነገሩን ያወቁ ነበርና ምን እንደሆነ በኋላ አስረዱኝ። ያን ቀን በአስመራ በሰሜን ምዕራብ በኩል ቪላጆ የሚባል ሰፈር፣ የሚካኤል ይሁን የገብርዔል ቤተክርስቲያን አለ። (የቱ እንደሆነ አሁን አላስታወስም)። የዚያ ቤተክርስቲያን ታቦት የሚወጣበት ቀን ነበር። ታዲያ ቤተክርስቲያኗ አካባቢ የሚኖሩ ነዋሪዎች ታቦቱ በነገሠበት ቀን ደግሰው በአካባባው ያሉትን ሁሉ ይጋብዙ ነበር። ይሄ ሥርዓት ነውእንግዲህ "ንግደት" የሚባለው።

ያኔ መኪና የለንም። በእግራችን ከአንድ ሰላሳ ደቂቃበኋላ ቪላጆ ደረስን። አራት ተማሪዎች ነበርን። በሰፈሩ ስንሽከረከር "ኑ ግቡ!" ብሎየሚጠራን ሰውአጣን። ለካ ኑሮ በጣምስለተወደደ እንደድሮ በየመንገዱ እየቆሙ"ብሉልን ጠጡልን" ማለት ቆሟል። "መቼምየዩኒቨርሲቲ ካፍቴሪያ ምግባችንን ትተን ባዶሆባችንን አንመለስም" ብለን ወደ አንዱቤት አመራንና አንኳኳን። "እንኳን አደረሳችሁ!" ስንል፣ አንዲት ያኔ ወደ አርባ ዓመት የሚጠጋት እናት፣ በእጇ አንድ ሕጻን ልጅ ታቅፋ ወጣችና "ግቡ! ግቡ!" አለችኝ በፈገግታ። የቤቱ በር ጠባብነበር። ጎንበስ ብለን ገባን። የነበረችዋን ጠረጴዛ ከበብናት። በትልቅ ትሪ እንጀራ ቀረበልን። ከዚያ ሴትየዋ ድስቱን አመጣችና ወጡን እንዳለ እንጀራውላይ ገለበጠችው። ብዙ ጊዜምአልፈጀብንምትሪውን ጠረግነው። ከዚያምበትላልቅ ጣሳዎች ጠላ አመጣች። ምን ልበላችሁምን የመሰለ መስተንግዶ ተደረገልን።

አስመራን ሳስብ፣ የአስመራ ነዋሪዎችን ሳስብ ያቺን ሴት አስባለሁ። ለእግዚአብሔር ፍቅር ስትል፣ እንግዳን በደስታየምትቀበል ትግረኛ ናት፤ ነገር ግን ከፊቷ ውስጣዊ ሠላምያላትና ሰውን የምትወድትልቅ ሴት ነበረች። ያኔ በትግሪኛ አይደለም ያናገርናት። "የኔ ዘር ናቸው" ብላ አልነበረምያስተናገደችን። ነገር ግን ትልቅ ሴት በመሆኗ እንጂ። የማያልፍ ነገር የለምና የዩኒቨርሲቲ ትምህርታችንን አጠናቀን የምረቃችን ቀን ደረሰ። ባጽዕ (ምፅዋ)በህዝባዊ ሓርነት ኤርትራ ግንባር ሥር ከወደቀ በኋላ በምፅዋና በአስመራ መሃከል ከሚገኝ አንድ የከፍታ ቦታ፣ "ግራፒ" እንለው የነበረ ከሩቅ የሚተኮስ መድፍ በየጊዜውአስመራ ከተማላይ ያርፍ ነበር። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ አስመራ መብረሩን አቁሞነበር። (የጦር አውሮፕላን ግን ማረፉን አላቆመም)። የኢትዮጵያ አየር መንገድ ስለማይበርም ቤተሰቦቻችን ለምረቃችን ከአዲስ አበባ ሊመጡአልቻሉም። ስለዚህ የምረቃ ሥነ ሥርዓታችን ብዙ አልጓጓንለትምነበር።

የምረቃችን ሥነ-ሥርዓት ቀን በወንዶች ሽንት ቤት ውስጥ ትልቅ ፈንጂ ፈነዳ። ያን ሰዓት ትልቅ ድንጋጤበዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ለጥቂት ደቂቃዎች ተፈጠረ። ወዲያው ሻዕቢያ የደስታ መግለጫመልዕክት ማስተላለፉ ነውብለን ቀልደን አለፍን። ከሩቅ በሚተኮስ መድፍ በግራፒ ተምሮ በፈንጂ መመረቅ ይሉታል ይሄ ነው። ያ ቀን ከፈንጂ ፍንዳታውሌላ የማልረሳው፣ በጣምልቤን የነካና ከኤርትራ ህዝብ ጋር ዘላቂ ፍቅር እንዲኖረኝ ያደረገ አስደናቂ ነገር ሆነ። ቤተሰቦቼ ከአዲስ አበባ ስላልመጡየምረቃ ልብሴን አውልቄ ወደ ዶርሚተሪ ለማምራት እየተዘጋጀሁ ሳለ ድንገት፣ አንዲት ሴትዮ አበባ ይዘውብቅ አሉ። 'ትዬ ዘይዳ ነበሩ። ትንሽ ቆይቶ ደግሞአንዲት አሮጊት ሴትዮ ሌላ እቅፍ አበባ ይዘውመጡ፡ አደይ ፀሐይቱ ነበሩ። ሁለቱምአይተዋወቁም። በአራት ዓመት የአስመራ ቆይታዬ የተወዳጀኋቸውእናቶች ናችው። 'ትዬ ዘይዳ እና አደይ ፀሐይቱ ከመምጣታቸውበፊት ብቻዬን የሆንኩ መስሎኝ ነበር። ግን ከአንድምሁለት እናቶች እንደ እናቴ ሆነውአበባ ይዘውበምረቃዬ ተገኙ።

እነዚህ ሁለት እናቶች እኔን ምረቃአስመልክተውዶሮ አርደውቤታቸውድግስ አዘጋጅተውነበር። ሁለቱምወደ ቤታቸውእንድመጣፈለጉ። ግራገባኝ። በኋላ አንዳቸው ጋር ምሳ ሰዓት፤ ሌላኛዋ ጋር ደግሞሲመሽ ሂጄ ከጓደኞቼ ጋር የተዘጋጀልኝን ድግስ ተካፈልኩ። አስመራን ሳስብ፣ የአስመራን ህዝብሳስብ ትዬ ዘይዳ እና አደይ ፀሐይቱን አስባለሁ። እነዚህ እናቶች በስጋ እናቶቼ አይደሉም። እንደነርሱ ትግሬ አይደለሁም። እንደነርሱየኤርትራ ተወላጅ አይደለሁም። የእነዚህን እናቶች የዋህነት፣ ፍቅርና ያላቸውን ፈሪሃ እግዚአብሔር ከተግባራቸውእናያለን። የእነዚህ እናቶች ደጎችና ለዘር ቦታየማይሰጡመሆናቸውን አይቻለሁ፤ እናንተምይህን ማየት እንደምትችሉ

አምናለሁ። እነዚህ እናቶች ባይወልዱኝም እናቶቼ ናቸው!እግዚአብሔር ባሉበት ቦታ ያክብራቸው! - አሜን !!!

የመጨረሻ ዓመት ተማሪ እያለን በአንድ ሃይስኩል (ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት)፣ ለሦስት ወር ማስተማር ነበረብን። ባርካ ተብሎ በሚታወቅ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመደብኩ። የተመደብኩበት ክፍል አስተማሪ ክፍሉ በጣም ረባሽ ክፍል እንደሆነ አስጠነቀቀኝ። በጣም ፈራሁ። ነገር ግን ማስተማሩን ስጀምር የተካሁት አስተማሪ ከነገረኝ የተቃረነ ሁኔታ ነው ያየሁት። ተማሪዎቹ በጣም የሚያዳምጡ፣ በአክብሮት ከተያዙ ብዙ ሊሠሩ የሚችሉ ሆነው ነበር ያገኟቸው። አስተማሪያቸውም ብሆን ጓደኞቼም ሆነው ነበር የተለያየነው። ያኔ ከተማዋ ችግር ላይ ነበረች። እንደዚያም ሆኖ ግን ከፊታቸው፣ ከሁኔታቸው ያየሁት ፍቅርንና ደስታን ነበር።

አስመራን ሳስብ፣ የአስመራን ህዝብ ሳስብ ያኔ ወርቃማ ዩኒፎርም ለብሰው የማስተምራቸውን ያዳምጡ የነበሩትን፣ ሳስረዳቸው ፊቴን ያዩ የነበሩትን የባርካ ተማሪዎችን አስታውሳለሁ። እርግጥ ነው ብዙ የሚያሳዝኑ ነገሮች በአስመራ አይቻለሁ። እርግጥ ነው ከተማዋ ያኔ መለስተኛ ጦር ግንባር ነበረች። እርግጥ ነው በየጊዜው ሳይታሰብ በሻዕቢያ የሚተኮስ መድፍ ባልተጠበቀ ቦታ ያርፍ ስለነበረ ብዙ ሰዎች አልቀዋል። እርግጥ ነው በደርግ ወታደሮች የተሠሩ ብዙ ግፎች ነበሩ።

ነገር ግን እንደዚያም ሆኖ የህዝቡ ፍቅር አሸንፎኝ ነው የጦር መሣሪያ በተሸከመ የጦር አውሮፕላን፣ መሣሪያ ላይ ተቀምጬ ከተማዋን የለቀቅሁት። አሁንም ለአስመራ ትልቅ ፍቅር አለኝ። አሁንም አስመራን ከአዲስ አበባ ቀጥሎ እንደ ከተማዬ ነው የማያት። አሁንም ያንን ህዝብ እንደ ህዝቤ ነው የማየው። አሁንም ኤርትራውያንን ከተቀረው ኢትዮጵያዊ እንደተለዩ ተደርጎ ሲታይ አያስደስተኝም።

በዚህ ምክንያት ነው የኤርትራን መገንጠል አጥብቄ የተቃወምኩት። አሁንም የምቃወመው። ለዚህ ነው ከመረብ ደቡብ ይኖሩ የነበሩ ወደ ኤርትራ፣ ከመረብ ሰሜን ይኖሩ የነበሩ ደግሞ ከኤርትራ በግፍ እንዲባረሩ መደረጉ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ነው የምለው። ለዚህ ነው የባድመ ጦርነት የወንድማማቾች የርስ በርስ ጦርነት እንጂ ከውጭ ኃይላት ጋር የተደረገ ጦርነት አይደለም የምለው። በአዲስ አበባና በአስመራ ዲሞክራቲክ መንግሥት ቢኖር በፍቅር፣ በውይይት፣ ለሁሉም በሚጠቅም መልኩ የኤርትራ ችግር ይፈታል የሚል ሙሉ እምነት አለኝ። ኤርትራም ከኢትዮጵያ ጋር ትዋሃዳለች። በሳባ ስቴዲየም ቺፖሊኒና ጊዮርጊስ ይጫወታሉ። በአዲስ አበባ ስፖርት ኮሚሽን ፊት ለፊት ከአስመራ የመጡ እንደ ተስፋጋብር አይነት ብስክሌተኞች የብስክሌት ጥበባቸውን ያሳዩናል። ስለዚህ ትኩረት በኤርትራውያንና በተቀረነው መሃከል ያለውን ያለፉት አሳዛኝ አስራ ሰባት ዓመታት የፈጠሯቸው ጠባሳዎች ላይ መሆን የለበትም።

ትኩረቱ፣ በአዲስ አበባና በአስመራ ህዝብን የሚያከብሩ፣ ለሕግ የበላይነት የሚገዙ መንግሥታት እንዲዘረጉ ማድረጉ ላይ መሆን አለበት። አቶ መለስ ዜናዊና ድርጅታቸው ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን፣ ቴዲ አፍሮን፣ ...የመሳሰሉ የሕሊና እስረኞችን በመፍታት፣ የህዝብን ጥያቄ እንዲያከብሩ፣ አቶ ኢሳያይስ አፈወርቂ ደግሞ የቀድሞ የአስመራ ዩኒቨርሲቲ የተፈጥሮ ሣይንስ ዲን የነበሩት ዶ/ር ክፍሉ ገብረመስቀልን፣ ፓስተር ኃይሌ ነእዝጊን፣ ፓስተር ተስፋጽዮን ሃጎስን፣ ...የመሳሰሉ በእምነታቸው ምክንያት የታሰሩትን በመፍታት፣ ከግትርና ከእልህ ፖለቲካ ወጥተው ለህዝብ ጥያቄ ቅድሚያ እንዲሰጡ ማድረጉ ላይ ትልቅ ግፊት መደረግ አለበት እላለሁ።